# የኢሕአፓና የኢትዮጵያ የትግል አንድነት
# በብዙ ሰፈር ታመነበት

*ከጀኔራል ሱናሚ*

*በአረብ ሕዝቦች እንቅስቃሴ ምክንያት የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ኃይሎችና የሕዝቡ ሁኔታዎች በያቅጣጫው በተለያዩ ሰፈሮች በውል መገምገማቸውን ከልዩ ምንጭ በምስጢር ተገልጾልናል።*

*በግምገማዎቹ መሠረት ሕዝቡና ኢሕአፓ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ የሚሰሩና ለበጎ ፖለቲካ የቆሙ ከመሆናቸው ጋር ባልተጠበቀ ሰዓት የፖለቲካ አመጽ ፈጥረው ያለውን መንግሥት እጅና ንብረት በቀላሉ በመማረክና ጉዳት ሳይከተል አገሪቱን አስተካክለው የመምራት ኃይልና ተቀባይነት እንዳላቸው ከዚሁ ምንጭ በተጨማሪ ተገልጿል።*

*ቀሪዎቹን የተቃዋሚ ድርጅቶችን ግን ለአገርና ለሕዝብ ሳይሆን ለገዛ ሥልጣናቸው ብቻ የቆሙ ወደ ትፋቱ እንደሚመለስ ውሻ ሽንፈታቸውን የመድገም እንጂ የፖለቲካ ብቃት የሌላቸው፣ ያለው መንግሥት አተላ በገንዳ ላይ ሞልቶ ጨው ነስንሶ ቢጠራቸው እንኳ ያን ለመላስ የሚሽቀዳደሙ ፌዘኞች አድርገው ተመልክተዋቸዋል።*

*ይህን በየአቅጣጫው በብዙ ሰፈር የታመነበትን ልብ ማለቱና አቋምን ማስተካከሉ ወቅቱ የሚጠይቀው የትግል መስመር ነው። በዚህ ግንዛቤ የፖለቲካ ታዛቢዎች፣ የሴራ ጠበብቶች፣ የሥነ-መንግሥትና የሥነ-ሥልጣን ሊቃውንቶች፣ ፖሊሲ አፍላቂዎች፣ ኮንሰልታንት ወዘተ... ሁሉ እንደተስማሙ ስለታወቀ አበሻ የምስራች እያልህ አሰላለፍህን አሳምር፣ ሰንደቅዓላማህን ከፍ አርገህ ይዘህ ከኢሕአፓና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር አብረህ ታገል።*

***ድል ለኢሕአፓና ለሕዝብ!***